ጠዋት በማለዳ

የወፎቹ ዜማ ከቤተስኪያን ደውል አብሮ ሲሰማ

የንጋቷን ፀሐይ በነጻነት ብርሃን ለኩሼ ቀናቴን

በኩራት የምቆም ቀና አርጌ አንገቴን

እንደ ማጀት ሞያ ጦር እያሰገሩ ጠላት ማሸነፉን

የነኩኝ እንደሆን በጸጸት አለንጋ በቅጣት ማከነፉን

ከኖረች ንግሥቴ ከእናቴ የተማርኩ

እንቢኝን  ዘማሪ ወኔዋን የወረስኩ

ከነኩኝ የማልምር ያገር ፍቅር ስሜት ልቤን ያከነፈኝ

የዛች የጀግናዋ የጣይቱ ልጅ ነኝ

ብልሃትን ከድፍረት ሰፍታ ከወኔዋ

የአገሯን ክብር ከፍ አርጋ ባ'ድዋ

ለማጀት ሲያጯት ጋሻና ጦር ታጥቃ በል በለው እያለች

ያልነበረ ታሪክ በደሟ ያተመች

ቅዬን ጉድ ያሰኘች አገር ያስገረመች ዓለም ያስደመመች

እናቴ ጀግና ነች

የጠላትን ወኔ ሜዳ ከትቢያ ላይ በድፍረት ጎትታ

አገር ማለት ምንድን ብሎ ለሚቀጣት አንድ ሕይወቷን ሰጥታ

ለእኔ ላንተ 'ሚሆን በተግባር የቆሞ ኑረት ያስተማረች

ሴት መሆን ስሙ ላይ የመሪነት ግርማን በግነት ያተመች

ጣይቱ ጀግና ነች

እኔም የእናቴ ልጅ ታሪክን ደጋሚ

በወረስኩት ወኔ የሩቁን ዓላሚ

ከማጀት ያለፈ ትውልድ የሚያነበው ታሪክ የምሰራ

የአገሬን ፍቅር በወኔ ኳሽቼ ሕይወት የምዘራ

ለነኩኝ የማልምር ያገር ፍቅር እምነት ልቤን ያከነፈኝ

ጀግንነትን ወራሽ የጣይቱ ልጅ ነኝ፡፡